# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው
ያስነብቡ!
አባዝተው
ያሰራጩ!

ቁጥር 217 ሐምሌ 5 2004 ገጽ 1

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ለነፃ ሲቪል ማኅበራትና ለሲቪክ እንቅስቃሴዎች ከፍተኛ ግምትና አክብሮት አለው። በሲቪክ ማኅበራት አማካይነት ታላላቅ የነፃነት ትግሎች መደረጋቸው ግንቦት 7 ያውቃል። በኢትዮጵያም ውስጥ የሲቪክ ማኅበራት ሚና ከፍተኛ እንደሆነ ያምናል። ሲቪል ማኅበራት የሚፈጥሩት ማኅበራዊ ካፒታል የአብሮነታችን ዋስትና እንደሆነ ይረዳል። ሲቪክ ማኅበራትን መፍጠርና ማጠናከር እና በሲቪክ ማኅበራት ውስጥ በንቃት መሳተፍ የትግላችን አንዱ አካል እንደሆነ ግንቦት 7 በጽኑ ያምናል። ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## በዘረኛው መለስ ዜናዊ ጤንነት ምክንያት ሰኔ 30 መዘጋት የተሳነው የወያኔ ፓርላማ በትናትናው ዕለት ልዩ ስብሰባ አድርጎ ሌላ አፋኝ የቴሌ ህግ አጸደቀ

ሰኔ 30 ቀን መዘጋት የነበረበት የወያኔ ፓርላማ በትናትናው ዕለት ልዩ ስብሰባ አካሂዶ አስቸኳይነቱ አጠያያቂ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ሲነጋገር እንደዋለ የግንቦት 7 ዘጋቢ ከሥፍራው በላከ ዜና ገለጸ።

99 ነጥብ ስድስት በመቶ ምርጫ አሸንፊያለሁ በማለት ካድሬዎቹን በምርጫ ሥም ፓርላማ ውስጥ የሰገሰገው መለስ ዜናዊ በትናንትናው ስብሰባ ላይ ሊገኝ ይችላል የሚል እምነት በበርካታ የፓርላማ አባላት ዘንድ እንደነበረ የዘገበው ዘጋቢያችን፤ በአለቃቸው አለመገኘት ብዙዎች ፊታቸው ላይ መደናገጥ ይነበብ እንደነበረ ገልጾአል።

የትናትናውን የፓርላማ ውሎ የተከታተሉ በርካታ የአገር ውስጥና የውጪ ፖለቲካ ተንታኞች እንደሚሉት ፓርላማው ተነጋግሮባቸው አጽድቆአቸዋል ካላቸው 5ቱ ደንቦች ውስጥ አንዳቸውም አጣዳፊ ወይም ልዩ ስብሰባ ሊያስጠራ የሚችል አይደለም።

ላለፉት 18 አመታት አንዴም ከፓርላማ ተብዬው መዝጊያ ስብሰባ ጠፍቶ የማያውቀው መለስ ዜናዊ በጤንነት ችግር ምክንያት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከህዝብ እይታ ብቻ ሳይሆን የቅርብ ሎሌዎቹ ከሆኑት የኢሃደግ ባለሥልጣናትም ተሰውሮ ስለሚገኝ በትናንቱ ስብሰባ ቢያንስ የጤንነቱ ሁኔታ ለፓርላማ አባላቱ ይነገራል የሚል ተስፋ በአንዳንዶች ውስጥ እንደነበረ ስማቸውን ለመግለጽ ያልተፈለገ አንድ የብአዴን አመራር አባል ለዘጋቢያችን ገልጸዋል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የሳውዲ አረቢያ ፖሊሶች አንዲት ኢትዮጵያዊት ሴትን እየገፈታተሩ መኪና ውስጥ ሲከቷት የሚያሳይ የቪዲዩ ምስል በድረ-ገጾች መለቀቁን ተከትሎ በዓለም ዙርያ ያሉ ኢትዮጵያዊያን በመለስ ዜናዊ አገዛዝ ላይ ያላቸውም ቁጭት እየገለጹ ነው

የሳውዲ አረቢያ ፖሊሶች አንዲት ኢትዮጵያዊ ሴትን እየገፈታተሩ መኪና ውስጥ ሲከቷት የሚያሳይ የቢዲዩ ምስል በድረ-ገጾች መለቀቁ ተከትሎ በዓለም ዙርያ ያሉ ኢትዮጵያዊያን በመለስ ዜናዊ አገዛዝ ላይ ያላቸውም ቁጭት እየገለጹ ነው። ወጣቷ በሳውዲ ውስጥ በቤት ሠራተኝነት የምትደዳደርና በአሰሪዋ የሚፈጸምባትን ግፍ ሸሽታ የወጣች ትሆናለች ተብሎ ተገምቷል። ቢዲዮው እንደሚያሳየው ወጣቷ የድረሱልኝ ጥሪ ብታሰማም የሚደርስላት ግን አላገኘችም። ወጣትዋ በከፍተኛ ድምጽ ብታለቅስም በርካታ ፖሊሶችና የሲቪል ልብስ የለበሱ ሰዎች ሰብዓዊ ክብሯን በሚያዋርድ ሁኔታ የወሳንሳ ተሸክመው መኪና ውስጥ ሲከቷት ይታያል። አንዲት ብቸኛ ሴት ብዛት ባላቸው ፖሊሶችና የሲቪል ልብስ በለበሱ ወንዶች ስትንገላታ ማየት ልብን የሚሰብር ነው ይላሉ በፊልሙ ላይ አስተያየት የሰጡ ወገኖች።

ከወራት በፊት በተመሳሳይ ሁኔታ ኢትዮጵያዊቷ ዓለም ደቻሳ ሊባኖስ በሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ በራፍ ላይ ስትጎተት የሚያሳይ ፊልም ወጥቶ እንደነበር ይታወሳል። ዓለም ደቻሳ ይህ አስከፊ ጥቃት ከደረሰባት በኋላ ሆስፒታል ውስጥ የገዛ ራስዋን አጥፍታለች መባሉና አስከሬንዋን ከወራት በኋላ ወደ ትውልድ አገሯ ተልኮ መቀበሩ ይታወሳል። በዓለም ደቻሳ ላይ ጥቃት ካደረሱ ሰዎች አንዳቸውም አልተከሰሱም፤ ስለአሟሟቷም የተብራራ መግለጫ አለተሰጠም።

በዓለም ደቻሳ ላይ የደረሰው በደል በኢትዮጵያዊያን ላይ የፈጠረው ምሬት ሳይረግብ አሁን ደግሞ ተመሳሳይ ነገር መከሰቱ ኢትዮጵያዊያንን በእጅጉ አሳዝኗል።

በአባይ ግድብና በልማት ስም ገንዘብ ለመሰብሰብ ከአገር አገር የሚዘዋወሩ የመለስ ዜናዊ አገልጋይ ዲፕሎማቶች ምስኪን ኢትዮጵያዊያን በደል ሲደርስባቸው ድርሽ እንኳን የማይሉ መሆኑ ከፍተኛ ቁጣ እየቀሰቀሰ ነው። እነዚህ ሆድ አደሮች ሆዳቸው እስከሞላ ድረስ ኢትዮጵያዊያን በውጭ አገራት መከራ ቢደርስባቸው የሚደሰቱ መሆናቸው ተግባራቸው ይመሰክራል ተብሏል።

በተመሳሳይ ዜናም በቅርቡ ወደ ደቡብ አፍሪቃ በስደት ጉዞ (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

ግዜ
ግንቦት 7 ዜና

## የዘንድሮ የሶሻል ሳይንስ ተማሪዎች ምርቃ በተመራቂዎች ከፍተኛ ተቃውሞ ምክንያት የተያዘለት ፕሮግራም ሳይጠናቀቅ ተበተነ

ሪፖርተራችን ከአዲስ አበባ እንደዘገበው ተቃውሞውና ረብሻው የተነሳው በቋፍ ያለውን የተመራቂዎቹን ብሶት፣ በምረቃው ስነ ስርዓት ላይ ተገኝቶ ንግግር ያደረገው የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስትሩ ጁነዲን ሳዶ ኮብል ስቶንን በማንሳት በመነካካቱ ነው።

በወቅቱ ጁነዲን ከኮብል ስቶን ጠረባና ንጣፍ ስራ ተመራቂዎቹ እንዴት እንደሚጠቀሙና እንደሚያተርፉ በተለመደው ወያኔያዊ ቅጥፈት መዘብዘብ ሲጀምር እንደ መብረቅ የጮኸ፣ በፉጨትና በኳኩዋታ የታጀበ ድምጽ አዳራሹን በማናጋት ጀምሮ እስከ መጨረሻው መዝለቁን ዘገባው አመልክቷል።

ካፈርኩ አይመልሰኝ ያለው ጁነዲንም በጩኸቱ ውስጥ ምን እንዳለ ባይሰማም ጥቂት ለመናገር ሞክሮ ስላልተሳካለት ንግግሩን የጨረሰ በማስመሰል አቁሟል።

ተመራቂዎቹ የምረቃ ስነ ስርዓቱ ሳያልቅ የተቃውሞ ድምጻቸውን እያሰሙ አዳራሹን ለቀው የወጡ ሲሆን አብዛኞቹ የብስጭት ስሜት ይነበብባቸው ነበር።

የተማሪዎቹን የተቃውሞ ድምጽ በመስማት ከግቢው ውጪ ተሰባስበው ይመለከቱ የነበሩ ሰዎችም በእንዲህ ዓይነቱ የደስታ ቀን እንዲህ ዓይነት ብስጭት መመልከት በዕጅጉ የሚያሳዝን ከመሆኑም በላይ ይህ ምናልባት በዓለም የመጀመሪያው ሊሆን ይችላል ሲሉ መደመጣቸውም ተዘግቧል።

ዘጋቢያችን ያነጋገራቸው ተመራቂዎች ስለ ሁኔታው ሲገልጹ ልክ ተቃዋሚዎችንና የግል ጋዜጣ አዘጋጆችን ሊያስሩ ሲፈልጉ እንደሚያደርጉት ሰሞኑን በቴሌቪዥን ስለ ባለዲግሪ ኮብል ስቶን አንጣፊና ይህንን የስራ እድል ለዩኒቨርስቲ ተመራቂዎች ስላዘጋጀው ልማታዊ መንግስት ሲያደነቁሩን የነበረውን ማንም ህሊና ያለው ሰው ሊቀበለው የማይችለውን ፕሮፓጋንዳ ትልቁ እበላ ባይ ካድሬ ጁነዲን በዚህ ቀን ሊደግምልንና ሞራላችንን ሊነካ ሞከሯል።

ይሁንና ቀድሞውንም ብስጭቱንና ተቃውሞውን እንዴት በጋራ እንደሚገልጽ ሲያስብ ለነበረው ተመራቂ ብሶቱን በመቀስቀስ ምቹ ሁኔታ በመፍጠር በግልባጩ የራሱ ሞራል ተከስክሶ ወርዷል ብለዋል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## በደቡብ ሱዳን አንደኛ አመት የነጻነት በዓል ላይ ይገኛል ተብሎ በመገናኛ ብዙሃን የተነገረው ዘረኛው መለስ ዜናዊ በጤንነት ችግር ምክንያት ሳይገኝ እንደቀረ ታወቀ

ደቡብ ሱዳን ነጻነቷን የተቀዳጀቺበት የመጀመሪያው አመት በአል አከባበር ላይ ይገኛሉ ተብለው ከጠበቁት የጎሬቤት አገሮች መሪዎች አንዱ የሆነው መለስ ዜናዊ ከትናንት በስቲያ ተከብሮ በዋለው የደቡቦች የነጻነት በዓል ላይ አለመገኘቱ ታውቆአል።

ቢቢሲን ጨምሮ በርካታ የአፍሪካ ሚዲያዎች የመለስ ዜናዊን በበዓሉ ላይ መገኘት በ እርግጠኝነት ዘግበውት የነበረ ቢሆንም በአመታዊ የፓርላማ ተብዬ ሸንጎ መዝጊያ ሥነሥርአት ላይ መገኘት እንደተሳነው እየታወቀ ለምን በደቡብ ሱዳኑ የነጻነት በዓል ላይ ሊገኝ ይችላል ተብሎ ለአለም አቀፍ ሚዲያ መረጃ እንደተሰጠ የሚያውቅ የለም።

እንደ አንዳንድ የፖለቲካ ተንታኞች ግምት መለስ አሁን ያለበትን የጤንነት ደረጃ በቅርበት የሚያውቁ ጥቂት የህወሃት አመራር አባላት ብቻ እንደሆኑና እነርሱም ቢሆኑ ሚስጥሩን ለመጠበቅ ሲሉ መረጃ ለማንም የማይሰጡ በመሆናቸው በማስታወቂያ ሚንስቴርና በውጪ ጉዳይ ሚንስቴር ውስጥ ያሉ የሥራ ሃላፊዎች ከመረጃ እጥረት ለውጪ ሚዲያ በሚሰጡት አስተያየት እንዲህ አይነት የተሳሳተ ዘገባ ሊሰራጭ ችሎአል።

በህወሃት መሪዎች መካከል የሚንሸራሸሩትን ምስጥር ነክ ነገሮች ወደ በታች ሹማምንቶች ቀርቶ በሚንስተርነት ደረጃ ላይ ለተመደቡትም ቅጥረኞች እንደማይደርስ ሽመልስ ከማል በቅርቡ የጠቅላይ ምንስትሩን ጤንነት አስመልክቶ የሚደረጉ ዘገባዎች የኢሳት ፈጠራ ወሬዎች ናቸው ማለቱ፤ እንዲሁም የስካይፒ መከልከልን አስመልክቶ እንዲሁ ሽመልስ ውሼት ነው ባለ ማግሥት ህወሃቶች ጉዳዩን ይፋ ማድረጋቸው እና በአንድ ወቅት ስለ አሜሪካ ድምጽ ሬዲዮ መታፈን ሽመልስ ከማል ሃሰት ነው ብሎ ለመገናኛ ብዙሃን የሰጠውን መግለጫ እራሱ መለስ ዜናዊ በአደባባይ እውነት መሆኑን መናገሩ የመሳሰሉትን ይጠቅሳሉ።

የወያኔ ውጪ ጉዳይ ሚንስቴር በደቡብ ሱዳን አንደኛ የነጻነት በዓል ላይ የኢትዮጵያ ል ዑካን የተገኘ መሆኑን ይፋ ያደረገ ቢሆንም የልዑካኑን ቡድን በማን እንደተመራና ስንት ሰዎች እንደሆኑ ከመናገር ተቆጥቦአል።

(ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

# ለሲቪል ማኅበራት ነፃነት የምናደርገው ትግል ለአገራችንና ለህልውናችን የምናደርገው ትግል አካል ነው!!!

በመለስ ዜናዊ የሚመራው ዘረኛ ቡድን አገራችንን ከተቆጣጠረበት ጊዜ ጀምሮ ነፃ ማኅበራትን ለማጥፋት ያልፈነቀለው ድንጋይ የለም።

አገዛዙ ሥልጣን እንደያዘ በራሱ አምሳል የፈጠራቸውን አሻንጉሊት ማኅበራትን ያደራጀው ለወጣቶችና ለሴቶች ነበር። በእነዚህ አሻንጉሊት ማኅበራት አማካይነት ነፃ የወጣቶችና ነፃ የሴቶች ማኅበራት እንዳይቋቋሙ መንገዱን ዘጋ። ከዚያ ቀጥሎም የሙያ ማኅበራት አንድም ሳይቀሩ በአገዛዙ ካድሬዎች ተጠለፉ፤ ከፊሎቹም እርስ በርሳቸው እንዲበጣበጡ በማድረግ እንዲዳከሙ ወይም እንዲፈርሱ ተደረጉ። ግብረሰናይ ድርጅቶች “በህግ” ሰንሰለት ታሰሩ። የእምነት ተልዕኮ ለማሳካት ሲባል የተቋቋሙ ማኅበራትም ከወያኔና ጋሻ ጃግሬዎቹ ጋር ካልተሞዳሞዱ “ፀረ-ሰላም”፣ “ፀረ-ልማት” እየተባሉ ተዋከቡ። ዛሬ በሃገራችን የወያኔ ቁጥጥር ወደ ሰንበቴዎች፣ እድሮችና እቁቦች ወርዷል። በዚሁ ከቀጠለ የቡና ተርቲቦችም መፈንጫው ይሆናሉ።

የወያኔ አፈና ከሃገር ቤትም አልፎ ወደ ውጭ አገራት መዛመቱ በእጅጉ ሊያሳስበንና ሊያስቆጣን የሚገባ ጉዳይ ነው። በነፃነት የመደራጀት መብታችን በተገደበ መጠን እንደማኅበረሰብ የመዝለቃችን ዋስትና የሆነው ማኅበራዊ ካፒታላችን እየሟሸሸ እንደሆነ እናውቃለን። የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ነፃ ማኅበራትን በአጠፋ ቁጥር የማኅበራቱ በጎ ተግባራት ከመሰናከሉ በተጨማሪ በአባላቱ መካከል ሊዳብር ይችል የነበረዉ መቀራረብና መተማመን መጥፋቱ አገራችንን በእጅጉ ይጎዳል። ማኅበራዊ ካፒታልን ማውደም ግዑዝ ካፒታል (ለምሳሌ ድልድይን) ከማፍረስ እጅግ የባሰ ጉዳት ያስከትላል፡፡

ስለዚህም ነው “ለሲቪል ማኅበራት ነፃነት የምናደርገው ትግል ለአገራችንና ለህልውናችን የምናደርገው ትግል አካል ነው” የምንለው።

በዚህ ረገድ ሰሞኑን ሁለት አበረታች ኩነቶችን አስተውለናል። እነዚህም፤ አንደኛው ከወያኔ የባርነት “ፎረም” ራሳቸውን ነፃ ያወጡ ወጣቶች “የወደፊት ራዕይ የወጣቶች ማኅበር” የሚባል ነፃ ማኅበር ማቋቋማቸው መሰማቱ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያ ስፓርት ፌዴሬሽን በዳላስ ያደረገው ደማቅ ዝግጅት ነው።

ሀ) የወደፊት ራዕይ የወጣቶች ማኅበር

በተለያዩ ምክንያቶች አንዳንድ ለራሳቸው ክብር የሚሰጡ ዜጎች “ኢሕአዴግ” ከሚባለው ፀረ-ኢትዮጵያ ድርጅት ጋር መቆራኘታቸው እናውቃለን። እነዚህ ኢትዮጵያዊያን ህሊናቸው እየቆሰለ መሆኑን መገመት ቀላል ነው። ከዚህ በፊትም የኢሕአዴግ መታወቂያን ወርውረው ራሳቸው ነፃ ያወጡ መምህራን እና ሌሎች ባለሙያዎች መኖራቸውን ጠንቅቀን እናውቃለን።

የወደፊት ራዕይ የወጣቶች ማኅበር አባላት የፈጸሙት ግን በዚህም በላይ ርቆ የሄደ በመሆኑ በአርዓያነት ሊወደሱ ይገባል። እነዚህ ወጣቶች ከኢሕአዴግ ባርነት ራሳቸውን ነፃ ከማውጣታቸውም በላይ ነፃ የሆነ የራሳቸው አዲስ ማኅበር ለማቋቋም መንቀሳቀሳቸው ይበል የሚያሰኝ ነው።

የወደፊት ራዕይ የወጣቶች ማኅበር ለመደራጀት በርካታ ፈተናዎች ይገጥሙት ይሆናል። ሆኖም ግን የኢትዮጵያ ሕዝብና ታሪክ ከጎኑ ናቸው።

ለ) የሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያውያን ስፖርት

የሰሜን አሜሪካ የስፖርት ፌዴሬሽን ከተቋቋመ ሃያ ዘጠኝ ዓመታት ተቆጥረዋል። ፌዴሬሽኑ በእስከዛሬው ቆይታው የዘንድሮን ያህል ችግር የገጠመው እና የዘንድሮ ያህል የተሳካለት ጊዜ አልነበረም ማለት ይቻላል።

ዘንድሮ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በምስለኔዎቹና ተባባሪዎቹ አማካይነት ፌዴሬሽኑን ለሁለት ለመሰንጠቅ ሞክሮ የከሸፈበት ዓመት ነው። ያ ሳይሳካለት ሲቀር መለስ እንደተለመደው ለፌዴሬሽኑ ተለጣፊ ፈጠረለት። የዓመቱን የስፖርት ዝግጅት ኢትዮጵያዊው ፌዴሬሽን ኢትዮጵያዊያንን ዳላስ ውስጥ ሲጠራ የመለስ ዜናዊ ፌዴሬሽን ደግሞ በገንዘብ ድጎማ ጭምር በማማለል ለተደራቢ ዝግጅት ዋሽንግተን ውስጥ ጠራ። የመለስ ዜናዊ ምስለኔዎችና ተባባሪዎች ድፍረት ኢትዮጵያዊያንን አስቆጣ። እናም ኢትዮጵያዊያን በእልህ ጭምር በመሰባሰብ ወደ ዳላስ ተመሙ። ወደ ዳላስ መሄድ ያልቻሉ የዲሲና አካባቢው ነዋሪ ኢትዮጵያዊያን ደግሞ የወያኔን እኩይ ሴራ በሰላማዊ ሰልፍ በመቃወም የወያኔን የፈንጠዚያ ድግስ ወደ ተስካርነት ለወጡት።

ኢትዮጵያዊነትና እና ወያኔነት፤ ፍቅርና እና ጥላቻ፤ ገንዘብ እና ህሊና፤ ወዳጅነት እና ዘረኝነት፤ ነፃነት እና ባርነት ጎራ ለይተው በዳላስና በዋሺንግተን ተሰለፉ። የዳላሶቹ ኢትዮጵያዊነት፣ ፍቅር፣ ህሊና፣ ወዳጅነት፣ ነፃነት አሸናፊ ሆኖ ወጡ።

የዘንድሮዉ የሰሜን አሜሪካ ስፖርት ጥልቅ ትምህርት ሊቀሰምበት የሚገባ አቢይ ኩነት ነው።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ለነፃ ሲቪል ማኅበራትና ለሲቪክ እንቅስቃሴዎች ከፍተኛ ግምትና አክብሮት አለው። በሲቪክ ማኅበራት አማካይነት ታላላቅ የነፃነት ትግሎች መደረጋቸው ግንቦት 7 ያውቃል። በኢትዮጵያም ውስጥ የሲቪክ ማኅበራት ሚና ከፍተኛ እንደሆነ ያምናል። ሲቪል ማኅበራት የሚፈጥሩት ማኅበራዊ ካፒታል የአብሮነታችን ዋስትና እንደሆነ ይረዳል። ሲቪክ ማኅበራትን መፍጠርና ማጠናከር እና በሲቪክ ማኅበራት ውስጥ በንቃት መሳተፍ የትግልችን አንዱ አካል እንደሆነ ግንቦት 7 በጽኑ ያምናል።

ስለሆነም ግንቦት 7 የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ለሲቪክ ማኅበራት ማበብ፣ መጠናከርና መጎልበት የተቻለውን ሁሉ እገዛ ያደርጋል።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

## በዘረኛው መለስ ዜናዊ ጤንነት ምክንያት ሰኔ 30 መዘጋት የተሳነው የወያኔ ፓርላማ በትናትናው ዕለት ልዩ ስብሰባ አድርጎ ሌላ አፋኝ የቴሌ ህግ አጸደቀ . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

እንደ አመራር አባሉ አገላለጽ በመላው አገሪቱ ውስጥ በስፋት የተሰራጨውን ጉዳይ የህዝብ ተወካዮች ናቸው ለተባሉ የፓርላማ አባላት መሰወር ለምን እንዳስፈለገ ግልጽ አይደለም። ህወሃቶች በውስጣቸው የሚካሄደውን ማንኛውንም ነገር ምስጥር አድርገው ከህዝብና ከመገናኛ ብዙሃን ደብቀው መኖር የቻሉበት ዘመን ከምርጫ 97 ወዲህ ማከተሙን የተርዱት አይመስልም ያሉት እኚህ ሰው እድሜ ለኤርትራ ቲቪ የግንቦት 7ን ድምጽና ኢሳት ሬዲዮ ስርጭት ከጀመረ ጊዜ ወዲህ መረጃዎቹን እየተከታተሉ ለህዝብ ጆሮ የሚያደርሱ በርክተዋል ብለዋል።

ይህ በዚህ እንዳለ ባለፈው ሰኞ የታተመው ሰንደቅ ጋዜጣ የወያኔ ፓርላማ ሰኔ 30 ቀን 2004 ዓም ለምን እንዳልተዘጋ የፓርላማው የህዝብ ግንኙነት ሀላፊ የሆነቿውን ወ/ሮ አሰፉ ገ/አምላክን ጠይቆ ፓርላማው ሰኔ 30 መዘጋቱን እንዳረጋገጠቿለት ሆኖም በሕገ-መንግስቱ አንቀፅ 58 ንኡስ አንቀጽ 4 መሰረት ምክር ቤቱ በእረፍት ላይ በሚሆንበት ወቅት የምክር ቤቱ አፈ-ጉባኤ ስብሰባ ሊጠራ እንደሚችል ስለተደነገገ ከአሁን ቦኋላ ቀጣይ ስብሰባዎች እንደሚኖሩ እንዲሁም እስካሁን መጽደቁ በይፋ ያልተገለጸው የ2005 በጀትም ከሰሞኑ እንደሚጸድቅ መናገሯን ዘግቦአል።

## የሳውዲ አረቢያ ፓሊሶች አንዲት ኢትዮጵያዊት ሴትን እየገፈታተሩ መኪና ውስጥ ሲከቷት የሚያሳይ የቪዲዩ ምስል . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

የነበሩ ኢትዮጵያዊያን ቁጥራቸው ከ40 የሚበልጡት በሞዛምቢክ ባህር ውስጥ መስመጣቸው፤ ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ተመሳሳይ ቁጥር ያላቸው ዜጎች ከአገር ሸሽተው ወደ ደቡብ አፍሪካ ሲጓዙ ተደብቀው ድንበር ለማቋረጥ ሲሉ በታጨቁበት ኮንቴይነር ውስጥ በረሃብና በአየር እጦት መሞታቸው ይታወሳል።

የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በሚያደርሰው የፍትህ መጓደል እና የሃገራችን ሃብት በጥቂቶች በመያዙ ሳቢያ በሕዝባችን ላይ በደረሰው ሥር የሰደደ ችግር ምክንያት ኢትዮጵያዊያን በየአገሩ ተሰዳጆች ሆነናል። መለስ ዜናዊንና የዘረጋውን ሥርዓት ከጭንቅላታችን ካላወረድን በስተቀር ኢትዮጵያዊ ክብርን ማስመለስ አይቻልም ይላሉ በጉዳዩ ላይ አስተያየት የሰጡ ባለሙያዎች።

## የዘንድሮ የሶሻል ሳይንስ ተማሪዎች ምርቃ በተመራቂዎች ከፍተኛ ተቃውሞ . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

ሌሎች በበኩላቸው ከዚህ ዘረኛ ስርዓት ከዚህ የበለጠ ነገር መጠበቅ አይቻልም፤ የወያኔ መንግስት ጸረ ኢትዮጵያ መንግስት ነው፤ በመሆኑም ባለ ዲግሪ ጎዳና ተዳዳሪና ድንጋይ አንጣፊ ዜጎችን በማምረት ሞራሉ የተነካ ትውልድ ማፍራትን ዋነኛ ግቡ አድርጎ የሚንቀሳቀስ ነው፤ እናም የተሻለች ሀገርና ነጻነት ያለው የተማረ ዜጋ የምንፈልግ ከሆነ ጸረ ኢትዮጵያና ጸረ ኢትዮጵያዊያን የሆነውን ዘረኛ የወያኔ ስርዓት ነገ ዛሬ ሳንል አሁኑኑ በጋራ ትግል ልናስወግደው ይገባል ሲሉ አብራርተዋል።

ጸረ ህዝብ የሆነው ወያኔ ቁንጮ መለስ ዜናዊ በአንድ ወቅት ምንም እውቀት ባይኖረውም የወያኔን ዓላማ እስካስፈጸመ ድረስ በየትኛውም የሀላፊነት ቦታ እንሾመዋለን ማለቱና ይህንንም ተከትሎ የመዋቅር ማሻሻያ፣ የመሰረታዊ ስራ ሂደት ለውጥ ወዘተ በሚል ሰበብ በርካታ አንቱ የተባሉ ባለሙያዎች ከየመስሪያ ቤቱ ተባረው ብቃት በሌላቸው ካድሬዎች መተካታቸውን መዘገባችን ይታወሳል።

## የትግራዩን ገዢ ጉጅሌ ከሥልጣን ማባረር ሃገራችንን ከድንቁርና ነፃ የማውጣት ትግል አካል ነው!!!

የግንቦት 7 ድምጽ በርዕሰ አንቀጽ ቁጥር 133 አውጥቶት የነበረ

የሰለጠነ የሰው ኃይል ለልማት ከሚያስፈልጉ ግብዓቶች ቀዳሚው መሆኑ የሚያከራክር አይደለም። የልማት ፍሬዓማነት መለኪያ ከሆኑ አመልካቾችም አንዱ የሰለጠነ የሰው ኃይል የመፍጠር አቅም መገንባቱ ነው።

ሃገር እንድትበለጽግ ከተመጽዋችነትና የበታችነት መንፈስ መላቀቅና በራስ የመተማመን ስሜት መገንባት ይገባል። በራስ የመተማመን ስሜት የሚገነባው ደግሞ የራስ የሆነን ነገር በማክበር እና የራስን አቅም በመገንባት ነው። ይህም ደግሞ የሰለጠነ የሰው ኃይል መገንባትን፤ የተገነባውን መንከባከብን እና በአግባቡ መጠቀምን ይጠይቃል።

በዛሬዋ ኢትዮጵያ እየሆነ ያለው ግን የዚህ ተቃራኒ ነው። የትግራዩ ገዢ ጉጅሌ ኢትዮጵያዊውን ባለሙያ አያምንም። ኢትዮጵያዊ ባለሙያ ወይም ምሁር በጉጅሌው ካድሬዎች የሚንጓጠጥ፣ የሚጉላላ፣ የሚሰደብና የሚረገጥ እንጂ በአገሩ ጉዳይ የሚናገር፤ ስለ አገሩ የሚቆረቆር መሆን አይችልም። ኢትዮጵያዊ ባለሙያና ምሁር የካድሬ መጫወቻ ነው። የትግራዩ ጉጅሌ በጉልበት ሥልጣን ከያዘበት እለት ጀምሮ በእውቀትና በአዋቂዎች ላይ ዘምቷል።

እውቀትንና አዋቂዎችን ከማጥፋት ጎን ለጎን ደግሞ የራሱን ትንሽነት መደበቂያ መንገድ ፈጥሯል። “እኔም የተማርኩና የተመራመርኩ ነኝ” በማለት የዝቅተኝነት መንፈሱን ለማስታመም ጉጅሌው ራሱን በግዢ በተገኙ የትምህርት ማስረጃዎች አንበሻብሿል። የሃገሪቱ የትምህርት ሥርዓትም እሱ ራሱ የያዛቸውን ዓይነት ባዶ ወረቀቶችን ማደያ አድርጎታል። በዚህም ምክንያት አገራችን ውስጥ ሙያም ባለሙያም ተዋርዷል። በዘመነ ወያኔ “የተማረ ነው” መባል የስድብ ያህል አሳፋሪ ሆኗል።

በእውቀትና በአዋቂዎች ላይ የተደረገው ዘመቻ ውጤት በየእለቱ እያየነው ነው፡-

- ፍርድ ቤት ስንሄድ በስልክ እየተነገረው የሚፈርድ ዳኛ ችሎት ላይ ተኮፍሶ እናገኛለን፤
- የፍሳሽ ማውረጃ የሌላቸው ፎቆችን እየገነባ ያለ መሃንዲስ በጥበቡ ብዛት ይራቀቅብናል፤
- መርፌ በወጉ የማይወጉ ሃኪሞች በበሽተኞች ላይ ይዘባበናሉ፤
- ለተማሪዎቻቸው የሰጡትን ፈተና እራሳቸው ቢፈተኑ የማያልፉ መምህራን “ከኔ ባላይ ላሳር” ሲሉ ይገኛሉ።

በእንዲህ ዓይነት “የተማረ” ሰው ኃይል እድገት ሊመጣ ቀርቶ አሉበት መቆየትም አዳጋች ነገር ነው።

በአንፃሩ ቀድሞ የነበረው የትምህርት ሥርዓት በርካታ ድክመቶች የነበሩበት ቢሆንም በሙያቸው የተከበሩ ጥቂት ምሁራንን አፍርቷል። የመጀመሪያው አፍሪቃዊ አይሮፕላን አብራሪ፣ የመጀመሪያው አፍሪቃዊ የስልክ ቴክኖሎጂ ባለሙያ፣ የመጀመሪያዎቹ አፍሪካዊያን የስነ-መንግሥት ምሁራን ኢትዮጵያዊያን ነበሩ። በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ብቻ ሳይሆን በቴክኒክ ኮሌጅ የሚሰጡ ትምህርቶች በሰለጠኑ አገሮች ከሚገኙ ተቋማት ጋር መሳ ለመሳ የሆነ ተቀባይነት ነበራቸው። ምሩቃኑም ሙያ ብቻ ሳይሆን የአገር ፍቅር ስሜት የተላበሱ ነበሩ። እነማንዴላን ጨምሮ ኢትዮጵያ ለብዙ አፍሪካዊያን አርዓያ ነበረች። አሁንም ቢሆን የዚያ ወቅት አሻራ ያረፈባቸው ኢትዮጵያዊያን ባለሙያዎች አሉ። እነዚህ ባለሙያዎች የሚገኙት ግን አሜሪካና አውሮፓ እና ሌሎች አገሮች ውስጥ እንጂ ኢትዮጵያ ውስጥ አይደለም። ሙያቸውን ጠንቅቀው ያወቁ፤ በራሳቸው የሚተማመኑ ባለሙያዎች ሁሉ ተገፍተው አገር ለቀው እንዲሰደዱ በመደረጋቸው ኢትዮጵያ ልትመካባቸው የሚገቡ ባለሙያዎች የሚገኙት በውጭ አገራት ውስጥ ነው።

የትግራዩ ገዢ ጉጅሌ በየክልሉ ለህንፃዎች የዩኒቨርስቲነት ስያሜ መስጠቱን እናውቃለን። ወደ እነዚህ ህንፃዎች የሚመላለሰውም ወጣት ቁጥር በብዙ መጨመሩ እውነት ነው። ሆኖም ባለሙያ ሲያፈሩ ግን አልታዩም፤ ለዚህ ተግባር የተፈጠሩም አይደሉም።

የትግራዩ ገዢ ጉጅሌ ያለበትን የእውቀት ማነስ የህዝብ ንብረት ለመሸጥ በምክንያትነት ሲያቀርብ መስማት ደግሞ ሌላው አስገራሚ ነገር ነው።

ለምሳሌ:-

- መሬትን በገፍ ለመሸጥ የሚያቀርበው ምክያት “ግብርናውን የማዘመን አቅምም ችሎታም የለንም” የሚለው እንደሆነ ልብ ይሏል። “ኢትዮጵያዊያን የግብርና ባለሙያዎች የት ገቡ?” ብሎ መጠየቅ አይቻልም። እንዲያም ሆኖ ግን “የግብርና ባለሙያዎችን በገፍ እያሰለጠንኩ ነው” እያለ ይቦተልካል።
- “የማዕድን ሃብታችን ለማልማት የሚጠይቀው እውቀትና አቅም የለንም” የሚለው ሰበብም ቱጃሩን እየጠቀመ እንደሆነ የኢትዮጵያ ህዝብ የሚያውቀው ጉዳይ ነው። ዛሬ የአገራችን የወርቅ ማዕድን በቱጃሩ ግለሰብ እጅ ውስጥ ገብቷል።
- አሁን ደግሞ “የማኔጅመንት ባለሙያ የለንም” በሚል ሰበብ ኮርፓሬሽኖችን መሸጥ ተጀምሯል። የኢትዮጵያ ቴሌኮሚኒኬሽን ማኔጅመንት ለፈረንሳይ ኩባንያ መሰጠቱ በመሬት የተጀመረው ሽያጭ ወደ ኩባንያዎች የመምጣቱ መርዶ ነጋሪ ነው። የሚቀጥሉት ተረኞች የኢትዮጵያ አየር መንገድ፣ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ እና የኤለክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እንደሚሆኑ መጠበቅ ይቻላል።

ግንቦት7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ይህ በድንቁርናው በመኮፈስ ላይ ያለው፤ ፀረ-እውቀት እና ፀረ-አዋቂ የሆነው የትግራዩን አምባገነን ገዢ ካስፈነብን የአገር ውስጥ ቅኝ አገዛዝ ነፃ እስካልወጣን ድረስ የኢትዮጵያ ትንሳኤ ሊኖር ይችላል ብሎ አያምንም። ስለሆነም የትግራዩን አምባገነን ገዢ ጉጅሌ በጋራ አስወግደን ሃገራችን ከገባችበት የድንቁርና አዘቅት እናውጣ እንላለን።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!**

## መለስ ዜናዊ የመንግሥት ሌቦች ባላቸው ላይ በተግባር የሚታይ እርምጃ ባለመውሰዱ ሌብነት መስፋፋቱን ሪፖርተር ገለጸ

የወያኔው መንግስት ቁንጮ መለስ ዜናዊ መንግስቴ በሌቦችና በሙሰኞች የተሞላ ነው እያለ እርምጃ አለመውሰዱ ብትሰርቁም፣ ብትዘርፉም፣ ሀገር ብትሸጡም፣ ህዝብ ብትበድሉም የሚነካችሁ የለም የሚል አደገኛ መልእክት ያለው ነው ሲል አፍቃሪ ወያኔ የሆነው ሪፖርተር ገለጸ።

እንዲህ ዓይነቱ ነገር ለሌቦቹና ለሙሰኞቹ አይዟችሁ በርቱ ተበራቱ የሚል የማበረታቻና የአድናቆት የድጋፍ የምስክር ወረቀት መስጠት ነው ያለው ጋዜጣው ለወንጀለኞቹ ብቻ ሳይሆን ለሕዝብም የተሳሳተ መልዕክት ማስተላለፍ ነው - ሙስናን ብትጠላም፣ ብትዘርፍም፣ ብትበድልም፣ ሌቦቹና ሙሰኞቹ ከአንተ በላይ ናቸውና አታጋልጣቸው፣ አትታገላቸው፣ አሜን ብለህ ተገዛ የሚል ይዘት ያለው በማለት አክሏል።

ይህ "ሙሰኞች ብፁዓን ናቸው፤ ፀረ ሙሰኞች ኃጢአን ናቸው "የሚል ውስጣዊ ይዘት ያለው ጽንሰ ሀሳብ ተሸክሞት እየተጓዘ ያለውን የወያኔ ስርዓት ለአደገኛ በሽታ በማጋለጥ በስብሶ በድን እንዲሆን እያደረገው መሆኑን በመግለጽ አስጠንቅቋል።

ወያኔ በራሱ ሌባና ሙሰኛ አባላት መንግስቱ እየተቦረቦረ መሆኑንም እንዲህ በማለት አብራርቷል። ሌቦችና ሙሰኞች ህዝቡን ብቻ ሳይሆን መንግስትንም የሚከዱ፣ የሚሸጡና የሚለውጡ ናቸው፤ ምክንያቱ ደግሞ መፈክራቸው"የተሻለ ካለ በጨረታው አንገደድም" ነው ያለው ሪፖርተር፣ የተቦረቦረ መንግስት - የተበደለ፣ የተረገጠ፣ የተሸጠና የተለወጠ ህዝብ ይዞ ሀገር መምራት እንደማይችል በማመላከት ስርዓቱ ከመሞቱ በፊት እድሜ ማራዘሚያ እዲያፈላልግ ለመምከር ሞክሯል ።

በዚህ ጉዳይ ላይ ያነጋገርናቸው አንድ አስተያየት ሰጪ እንዳሉት መለስ ዜናዊ ተራ የፖለቲካ ትርፍ ያገኘ መስሎት "የመንግስት ሌቦችና ሙሰኞች ቢልም" አዜብ መስፍንና ስብሀት ነጋን የመሳሰሉ የሙስና ነገስታትና ሌቦች እያሉ ተጨባጭ ርምጃ ይወስዳል ማለት ዘበት ነው። ለዚህ ደግሞ ወያኔ ያፈነገጡ አባላቱን፣ ደጋፊዎቼ አይደሉም የሚላቸውን የመንግስት ሰራተኞችና ነጋዴዎች ለመምታት ባቋቋመው ጸረ - ሙስና ኮሚሽኑ በሙስና ላይ አስጠናሁት ያለው "በኢትዮጵያ ሙስና ያለው በከፍተኛ የመንግስት አካላት ዘንድ ሳይሆን በመካከለኛና በዝቅተኛው ሰራተኛ ዘንድ ነው" የሚል መደምደሚያ ይዞ ብቅ ያለውን ዓይን አውጣ አስገራሚ ጥናት መመልከት ብቻ በቂ ነው ብለዋል።

የደቡብ ክልል ፕሬዘዳንት ሺፈራው ሽጉጤ በሙስና ሲገመገም እኔን ከጠየቃችሁኝ አዜብ መስፍንም አብራኝ ትጠየቃለች በማለቱ ግምገማው እንዲቋረጥ መደረጉ ግንቦት ሰባትን ጨምሮ በልዩ ልዩ ሚዲያዎች መዘገቡ ይታወሳል

## በደቡብ ሱዳን አንደኛ አመት የነጻነት በዓል ላይ ይገኛል ተብሎ በመገናኛ ብዙሃን . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

ሜክሲኮ ውስጥ በቅርቡ ተካሂዶ በነበረው የቡድን 20 ስብሰባ ላይ ቆሌ ርቆትና ስጋው አልቆ የታየው መለስ ዜናዊ ከሜክስኮ መልስ በቀጥታ ወደ ብራስል ቤልጂዩም ለህክምና ጎራ ብሎ ኬሞ ቴራፒ የተባለውን የካንሰር ህክምና ሲያደርግ እንደነበረ መዘገባችን ይታወሳል።

በጸረ ኢትዮጵያ አቋሙ የሚታወቀው ይህ ሰው ከአቅም በላይ የሆነ የጤንነት ችግር ላይ መውደቁን ከሚያመለክቱ የአካልና የመንፈስ ብቃት ጉድለት በተጨማሪ የዕለት ተዕለት ሥራዉን ማከናወን በማይችልበት ደረጃ ላይ መሆኑ በዚህም ምክንያት ባለፈው ሳምንት የፓርላማ መዝጊያ ላይ መገኘት አለመቻሉ፤ ሴኔ 21 ቀን በፈጣራ ሥራ የላቀ አስተዋጾ ያላቸውን ይሸልማል ተብሎ በኢትዮጵያ ቴለቪዥንና ሬዲዮ ከታወጀ በኋላ ፕሮግራሙ ለአንድ ሳምንት መራዘሙ ቢነገርም በዚያም ላይ ባለመገኘቱ ፕሮግራሙን ለመሰረዝ መገደዱ እንዲሁም በደቡብ ሱዳን የነጻነት በዓል ላይ ለመገኘት ፕሮግራም ተይዞለት ሳይገኝ መቅረቱ ከሚጠቀሱ መረጃዎች ጥቂቶቹ ናቸው።

## የተጠናከረ የወያኔ ጥበቃ በሚካሄድበት አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በጠራራ ጸሃይ የባንክ ዘረፋ መካሄዱ ተዘገበ

ካዛንቺስ የሚገኘው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የአንድነት ቅርንጫፍ ሰኔ 17 ቀን 2004 ዓ.ም. ሌሊት ዝርፊያ ከተፈጸመበት ቦሃአላ ሁለት ሳምንት ባልሚላ ጊዜ ውስጥ በድጋሚ ለሁለተኛ ጊዜ ሰኔ 30 ቀን 2004 በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 3 ከወሎ ሠፈር ወደ ጐተራ በሚወስደው መንገድ ወንጌላዊት ሕንፃ ሥር የሚገኘው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጐተራ ቅርንጫፍን ዝርፊያ ሙከራ እንደተካሄደበት ታወቀ።

ማንነታቸው ባልታወቀ ሰዎች መዘረፉ በተረጋገጠው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የአንድነት ቅርንጫፍ የተዘረፈው ገንዘብ መጠን ከስድስት ሚሊዮን ብር በላይ መሆኑን ዘገባዎች ያመለክታሉ።

በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 3 ከወሎ ሠፈር ወደ ጐተራ በሚወስደው መንገድ ወንጌላዊት ሕንፃ ሥር የሚገኘው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጐተራ ቅርንጫፍን ላይ ሰኔ 30 ቀን 2004 ዓ.ም. ተደርጎ የነበረው የዝርፊያ ሙከራ ካዝናው አልከፈት በማለቱ እንደከሸፈና ቀደም ሲል የአንድነት ቅርንጫፍ መዘረፉን ሆኖም ስለዘረፋው ባለሥልጣናት መግለጫ ሊሰጡ እንዳልፈለጉ ሪፖርተር ባለፈው እሁድ እትሙ ገልጾአል።

የቅርቆስ ባንክ ዘረፋ ሙከራ ያካሄዱ ሃይሎች የባንኩን ጥበቃ ሠራተኛ መፀዳጃ ቤት ውስጥ አስረው ቆልፈውበት እንደተሰወሩና በማለዳው ለዘወትር ጽዳት ሥራ ቢሮው የተገኙት የፅዳት ሠራተኞች እንዳገኙት ሪፖርተር ይፋ አድርጎአል።

በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቅርንጫፍ ባንክ ካዝና ውስጥ ከአራት ሚሊዮን ብር የበለጠ ተቀማጭ ገንዘብ እንደማይኖር የገለጹት ምንጮቹ፣ ለስርቆት ገብተው የነበሩት ግለሰቦች ሌላ የባንክ ንብረት ይውሰዱ ወይም አይውሰዱ አለመታወቁን ተናግረዋል ብሎአል ሪፖርተር፡፡

በካዝናው ጥንካሬ ከዝርፊያ ስለተረፈው ገንዘብና አሥራ አምስት ቀናት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ለሁለተኛ ጊዜ ስለተደረገው የባንክ ዘረፋ ሙከራ ወንጀል ለማነጋገር፣ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ፕሬዚዳንት አቶ በቃሉ ዘለቀን፣ የባንኩን የቢዝነስ ዴቨሎፐመንት ኃላፊ አቶ ይስሐቅ መንገሻንና የሕዝብ ግንኙነት ማስተባበሪያ ኃላፊውን አቶ ፀጋዬ ደስታን ለማግኘት ሪፖርተር ያደረግነው ጥረት እንዳልተሳካ ገልጾአል።

ወያኔ ያለ የሌለውን የጥበቃ ሃይሉን በከፍተኛ ሁኔታ ባሰማራበት አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ እንዲህ አይነት አይን ያወጣ ዘረፋ መካሄዱ የሚያመለክተው ወያኔ በየመንገዱ በቡድን ቡድን ይሰማራቸው የፖሊስ፤ የመከላኪያና የደህንነት ሰራተኞች በሙስናና በአገር ሃብት ዘረፋ የተጨማለቀውን የወያኔ አገዛዝ ሥልጣን እድሜ ለማራዘም ሲሉ ተግተው የሚሰሩት የጥበቃ ሥራ እንደሌለ አመልካች ነው ተብሎአል።

እንደሪፖርተር ዘገባ በሁለቱም ባንኮች ላይ የተፈጸመው ዘረፋ ጠቅላላውን የባንክ ሰራተኞች እጅግ ከማሳሰብ አልፎ በሌሎች ባንኮች ላይ ተመሳሳይ ዘረፋ ሊካሄድ እንደሚችል ስጋት ፈጥሮባቸዋል።

## የዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ በፈጠረው ክፍፍል ምክንያት ተቻችለው ይኖሩ በነበሩ ጎሳዎች መካከል ደም እያፋሰሰ ያለው ግጭት ተባብሶ ቀጥሎአል። በቦረና ዞን በተነሳው ግጭት ከ40 በላይ ዜጎች አለቁ

በቦረና ዞን አሬሮ ወረዳ ውስጥ በገብራና በቦረና ጎሳዎች መካከል በተነሳ ግጭት ባለፉት ጥቂት ቀናት ውስጥ ከ40 ያላነሱ ሰዎች መገደላቸውን የግንቦት 7 ዘጋቢ ከስፍራው ካስተላለፈው ዘገባ ለማወቅ ተችሎአል። የወያኔ ዘረኛ ፖሊሲ በፈጠረው በዚህ የርስ በርስ አለመግባባት የተነሳው ይህ ግጭት ይህ ዜና በተጠናከረበት በዛሬው ዕለትም እንደቀጠለ ከመሆኑ አልፎ የሁለቱ ጎሳዎች ቀደም ሲል ከተጋጩበት ቦታ አልፎ አድማሱን እያሰፋ መምጣቱን ተያይዞ የደረሰን ዘገባ ያመለክታል።

ዘጋቢያችን የአካባቢውን ነዋሪዎች እማኝነት ጠቅሶ እንዳጠናከረው በእስካ ትናንቱ ግጭት ከገብራ ጎሳዎች ወገን 21 ከቦረና ደግሞ 19 ሰዎች ተገድለዋል። የአንድ ቋንቋ ተናጋሪ በሆኑ በሁለቱ ጎሳዎች መካከል የተነሳው ይህ የርስ በርስ ውጊያ አድማሱን አስፍቶ ሱልሉታ ወደሚባለው የያቬሎ አካባቢ ተስፋፍቷል።
ወያኔ ሥልጣን ከተቆጣጠረና አካባቢውን በራሱ ቅጥረኛ ሆድ አደሮች ማስተዳደር ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ቀደም ሲል በሰላም ተፋቅረውንና ተቻችለው ይኖሩ የነበሩ ሁለቱም ጎሳዎች ደም አፋሳሽ የሆነ ውጊያ በተደጋጋሚ አድርገዋል ተብሎአል።

አነግ በአካባቢው ይንቀሳቀሳል ብሎ የሚሰጋው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ሁለቱ ጎሳዎች እርስ በርስ በመጠራጠርና በመጋጨት አንዱ ሌላኛውን ለማጥቃት በሚያደርጉት የበቀል እርምጃ በነርሱ በኩል ወደ ውስጥ ሊገቡ የሚችሉትን የአነግ ታጋዮች መያዝ ወይም መቆጣጠር ይቻላል የሚል ስሌት እንዳለ የአካባቢው ሰዎች ይናገራሉ።

ወያኔ በአካባቢው ያሰማራው የመከላከያ ሰራዊትም ሆነ የፌደራል ፖሊስ በሁለቱ መካከል የሚደረገውን የእርስ በርስ መገዳደል ለማስቆም እስካሁን ያደረገው አንድም ጥረት አለመኖሩ በርካታ የአካባቢውን ተወላጆች አስቆጥቷል።
ከአራት ወራት በፊት የሶማሊ ተወላጆች በሆኑ ገሪዎችና የኦሮሞ ተወላጅ በሆኑት ቦረናዎች መካከል በተፈጠረ ግጭት በርካታ ሰዎች ማለቃቸው በሰፊው መዘገቡ ይታወሳል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ከጋሞ የክልል ጥያቄ ጋር በተያያዘ በአርባ ምንጭና አካባቢዋ ውጥረት መኖሩን ኢሳት በትናንትናው ዜና ዘጋባው ገልጾአል። ካለፈው ጥቂት ሳምንታት ወዲህ በሲዳማ ዞን የተነሳውን ተቃውሞ ተከትሎ ሰሞኑን በአርባ ምንጭና አጎራባች ወረዳዎች ተመሳሳይ ችግሮች እየታዩ መምጣታቸው ወያኔ በሰላም ተፋቅሮና ተቻችሎ በአንድነት ይኖር የነበረውን ህዝብ በመከፋፈል የሥልጣን ዕድሜውን ለማራዘም ሲል ያደረገው ጥረት መልሶ የራስ ምታት እየሆነበት መምጣቱን ያመለክታል የሚሉ በርካቶች ናቸው።

እንደ ኢሳት ዘገባ የፌደራል ፖሊስ አባላት በአርባ ምንጭ የተነሳውን ውጥረት ለማርገብ በአካባቢው መስፈራቸው እና እያንዳንዱዋን እንቅስቃሴ በመቃኘት ላይ መሆናቸው ታውቆአል።

የመለስ ዜናዊ አገዛዝ የፈጠረው ከጎሳ ጋር በተያያዘ የሚነሱ አለመግባባቶች በየጊዜው እየጨመረ መምጣቱን በሰፊው ይነገራል።

## የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር ሰራዊት ወያኔ የዋልድባን ገዳም ይዞታ ወደ ስኳር ፋብሪካነት ለመቀየር ያሰማራቸውን ቡልዶዘሮች ሙሉ በሙሉ ማውደሙ ታወቀ

ሰራዊቱ ርምጃውን የወሰደው ሰኔ 20 ቀን 2004 ዓ.ም ሲሆን በወቅቱ ሾፌሮቹ በመደናገጥ ከአካባቢው መሸሻቸው ታውቋል። ርምጃውን ተከትሎም የአካባቢው ምዕመናን ለሰራዊቱ ድጋፋቸውን እየገለጹ ሲሆን ይህንን ጸረ-ኢትዮጵያ ጠባብ የወያኔ ስርዓት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እንዳይመለስ አድርጎ ለማስወገድ በሚደረገው ትግል ውስጥ ለመሳተፍ ስሜታቸው መነሳሳቱን ገልጸዋል።

በማከልም ጸረ እምነት የሆነው የወያኔ መንግስት እምነታችንን ለመናድ እያደረገ ያለውን መፍጨርጨር በቁርጠኝነት እየተቋቋምን ባለንበት በዚህ ወቅት የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር ለሰነዘረው ጥቃት ያለንን አድናቆት እየገለጽን ይህን የጀግንነት ተግባር አጠናክሮ እንዲቀጥል እንጠይቃለን ብለዋል።

ግንባሩ ወደፊትም ተመሳሳይ ርምጃዎችን ባስፈላጊው ሰዓት በመውሰድ ከህዝቡ ጎን እንደሚቆም በማረጋገጥ ለህዝቡ ጥያቄ ፈጣን ምላሽ ሰጥቷል።

ወያኔም በበኩሉ የደረሰበትን ጥቃት ለመበቀል አራት የገዳሙን አባቶችና ሌሎች ቁጥራቸው በውል ያልታወቀ የአካባቢው ምእመናን በማፈን ለጊዜው ወዳልታወቀ ቦታ እንደወሰዳቸው ተነግሯል።

ከዚህ ሌላ ጸረ- ኢትዮጵያ ታሪክ የሆነው ወያኔ የጀመረውን ታሪክ የማውደም ተግባር አጠናክሮ ለመቀጠል ተጨማሪ ጦር ወደ አካባቢው እያጓጓዘ መሆኑን የአካባቢው ምንጮች ገልጸዋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር ተነስ! ታጠቅ! ዝመት! የሚሉ መፈክሮችን የያዙ በራሪ ወረቀቶችን በማይጸብሪ፣ በአደርቃይና በዛሪማ አካባቢዎች ማሰራጨቱ ታውቋል።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

<u>መካከኛ ሞገድ</u>:- በ 358 MB, በ 837 kHz
<u>አጭር ሞገድ</u>:- በ 31 MB በ 9700 KHz
**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**
**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 3፡30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።
<u>ማሳሰቢያ</u>:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org